# ኢትዮጵያን ያለፌደራሊዝም ማሰብ ይቻል ይሆን?

(ክፍል 2)

ዮናስ 07/11/14

እያወራን ያለነው ስለኢትዮጵያና ስለፌደራሊዝም ስርአት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሥርዓትንና የብዝሃነትን ጉዳይ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች እይታና በተለይም ከሰሞኑ እየተደመጡ ያሉ የውህደቱ ፕሮፖጋንዳዎችን በተመለከተ በክፍል አንድ መጣጥፌ ለማሄስ ሞክሬያለሁ፡፡ ክፍል አንድ ተቃዋሚዎቹ አሁን ካሉበት ተጨባጭ ሁኔታና እያሰሙን ከሚገኙት ፕሮፖጋንዳዎች አንፃር የተቃኘ ሲሆን በዚህ ክፍልም ኢትዮጵያን ያለ ፌደራሊዝም ማሰብ የማይቻልባቸውን እና የተቃዋሚዎቹ የውህደት ግርግር ፌደራል ስርአቱን ወደጎን የገፋ በመሆኑ የአንድ ሰሞን ወሬ ከመሆን እንደማያልፍ አመላክቻለሁ፡፡ ቀጥሎ የምንመለከተው አስተያየት ያለፌደራሊዝም የትኛውም ፓርቲ ቢሆን ኢትዮጵያን ማሰብ የማይችልባቸውን እውነታዎች ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ህብረ ብሄራዊ የፌደራል ስርዓት አንጹና መሰረታዊ መነሻ መላ የጠፋችው ተቃዋሚዎች እንደሚሉት ሳይሆን ለአያሌ ዘመናት በኢትዮጵያ ሰፍኖ የነበረውን የተዛባ የህዝቦች ግንኙነት በማስተካከል አዲስ የኢትዮጵያዊነት ህብርና ዝምድናን መመስረት ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከ80 በላይ የተለያዩ ማንነቶችን ያቀፈች ሃገር መሆኗን መቼም መካድ አይቻልም፣ እነዚህ ማንነቶች ባለፉት የዘውድና ወታደራዊ አገዛዝ ዘመናት ማንነታቸውን እንዲሸሽጉ ወይም ጨርሰው እንዲፍቁ የተገደዱበት ስርዓቶች የነበሩ መሆኑንም እንዲሁ፡፡ በነገስታቱ ዘመን የኢትዮጵያዊነት መለኪያ የራስ ማንነትን በመተው የገዢዎችን ቋንቋ፣ ባህልና ሃይማኖት መልበስ፣ ዘውዳዊ ስርዓቱ የደገፈውን ሁሉ መከተልና መስሎ መታየት የነበረ መሆኑንም ዛሬ ተቃዋዎቹ ሊክዱ ቢሞክሩም ታሪክ የመዘገበው እውነትና ይልቁንም የክህደታቸው መነሻ ይህንኑ ስርዓት መመለስ መሆኑን በርካታ የፖለቲካ ተመራማሪዎች ያረጋገጡትና በተግባርም አሁን ካለው ተጨባጭ እንቅስቃሴያቸው የተገነዘብነው ሃቅ ነው፡፡

በመሳፍንታዊ ስርዓተ-መንግስት አንድ ሃገር የመፍጠርና የማቃናት ሂደት አንድ ቋንቋ፣ አንድ ባህል፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ማንነትና አንድ ሃገር በሚል ፍልስፍና ማንነትን በማፈን የተከናወነ ሆኖ ከኢኮኖሚ ጭቆና ጋር በማስተሳሰር የተፈፀመ መሆኑም እሙንና ልካድህ ቢሉት የማይቻል ነው፡፡ በነገስታቱ ዘመን ሌሎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችም የማይታሰቡ ስለነበር የሥርዓቱ ፍፁማዊነት ‹‹ንጉሥ አይከሰስ ሠማይ አይታረስ›› በሚል ብሂል ይገለፅ እንደነበረም የቅርብ ጊዜ ትውስታና የኢትዮጵያ ታሪክ አካል ሆኖ በነገስታቱ ዘመን የታሪክ ድርሳናት ላይ የመጀመሪያ ገፅ የሰፈረ እውነት ነው፡፡ ይህንን ማንነታቸውን የነጠቀውን ሥርዓት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ለማስከበርና ለማስመለስ የጀመሩትን ተጋድሎ ተከትሎ በአቋራጭ ስልጣን የነጠቀው የደርግ አስተዳደርም ለጭቁኑ ህዝብ የቆምኩ ነኝ ብሎ ወንበሩን ካደላደለ በኋላ ትግሉን ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት አስከፊ ጭፍጨፋ መፈፀሙም የዚህ ትውልድ ታሪክ በመሆኑ እንዲረሳ የተለያዩ የስነልቦናና የታሪክ መፅሀፍት ትግሎች ቢደረጉም ሊሳካ አልቻለም፤ አይችልምም፡፡ ማንነትን የማስከበርና የማረጋገጥ የመብት ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ ማንሳት ይቅርና ማሰብ ራሱ በህይወት የሚያስቀጣ አምባገነናዊ ስርዓት የነበረ መሆኑን የሚክዱትና አሁን በአዲስ መልክ ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱት ሃይሎች አብዛኞቹ የዚያው አምባገነናዊ ስርዓት አካልና አጋፋሪ የነበሩ መሆናቸው በመሰረቱ አፅንኦት ከተሰጠው ክህደታቸውና አሁን የጀመሩት ግርግር መነሻ ግልፅ ይሆናል፡፡

ደርግ በመሳፍንታዊ ዘመን የነበረውን የአንድ ሃይማኖት የበላይነት በመሰረቱ ሳይቀይር ነገር ግን ለውጥ ያመጣ በማስመሰል (ማስመሰል የደርጉ ባህሪ ነውና) ሁሉም ሃይማኖቶች እምነታቸውን በነፃ እንዳያራምዱ አፍኗል፤ የሃይማኖት ተቋማትን ዘግቷል፤ በርካታ አማኞች አገራቸውን ጥለው እንዲሰደዱ አድርጓል፡፡ በደርግ ይህን ማድረግ ሂደት ውስጥ ዋና ተዋናይ የነበሩት ደግሞ ዛሬ ስለሃይማኖት እኩልነትና የእምነት ነፃነት ተቆርቋሪ መስለው የተከፈተውን በር፤ የተከበረውን ነፃነት ለመዝጋትና ለማፈን አጥብቀው እየታተሩ ስለመሆናቸው ከላይ በቀረበው ተጠየቅ መሰረት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ደርግ ሌላም ያስመሰለው ነገር አለ፡፡ የዘውዳዊ አገዛዙ የኢኮኖሚ ምንጭ የነበረውን መሬት በመንጠቅ የመሳፍንታዊ ሥርዓት መሰረት እንዲነቀል ያደረገ ቢሆንም ለገበሬዎች ያከፋፈለው መሬት ፍትሃዊነት የጎደለው የነበረ ከመሆኑም ባሻገር አርሶ አደሮች ምርታቸውን በገበያ ዋጋ እንዳይሸጡ የዋጋና የኮታ ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ሀብታቸውንና ዕውቀታቸውን

አሟጠው በተሻለ ምርታማነት እንዳይሰሩና ኑሯቸውን እንዳይለውጡ ነፃነታቸውን ያፈነ ስርዓት በመሆኑም ማስመሰሉ ይገለፃል፡፡ ዛሬም ከመሬት መሸጥ መለወጥ ጋር ተያይዞ የሥርዓቱን ‹‹በኢህአዴግ መቃብር ላይ›› አቋም የሚያንኳስሱና ለህዝብ የቆሙ በማስመሰል የእነርሱን ምቾትና ጥቅም ያስጠበቀ የነበረ የኢኮኖሚ ስርዓት ለመመለስ እየተጋ መሆኑን ምናልባት አማራጭ ከተባለም የሚያቀርቡትን የፖሊሲ አማራጮች የሰማነውና የማንበበው እድል የገጠመን ሁሉ ለማረጋገጥ አይከብደንም፡፡

በጥቅሉ ከፌደራሊዝም ፅንሰ ሀሳብ ጋር ተያይዘው የሚነሱት ያለፉት ሁለት ስርዓት አመታት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ማንነታቸው የታፈነበት በሃገራቸው እንደሁለተኛ ዜጋ በመታየታቸው በሃገራዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ድምፅ ማሰማት የተነፈጉበት፣ ተሹመው በሚመጡ ባለስልጣናት እንጂ በራሳቸው ልጆችና ቋንቋ እንዲመሩ ያልቻሉበት፣ ኢትዮጵያ የብሄሮችና ብሄረሰቦች እስር ቤት የነበረችበት ዘመናት የነበሩ መሆኑ አያከራክርም፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ህብረብሄራዊ የፌደራል ስርዓት ይመሰረት ዘንድ አንዱና መሰረታዊ ምክንያት ለመሆን በቃ፡፡

*የፌደራል ስርአቱ ለዘመናት ተዛብተው የቆዩ የብሄረሰብ ለብሄረሰብ ግንኙነቶችን ማስተካከል ዋናው መነሻ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?* የሚለውንም አጣመው የሚያቀርቡና ከሥርዓቱ እድሜ ማራዘም ጋር አያይዘው ለመሞገት የሚሹ ሃይሎች እንደቀደመው ሁሉ የተነጠቁትን ለማስመለስ ደፋ ቀና የሚሉቱ ቢሆኑም የእነዚህን አስመሳዮች ጠባይ ለሚያውቁቱ ግን አላማቸው ከአጣሞ ማየት ባለፈ ሌላ ምን ማለት እንደሆነ (ምን አላማ እንዳላቸው) በግልፅ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

“ያለፉት ሥርዓቶች የፈጠሯቸውን ግንኙነቶች ማስተካከል ማለት የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችን የሃይማኖት እኩልነትን ማረጋገጥ ማለት ነው” የሚለው የፌደራል ስርአተ-መንግስቱ የመጀመሪያው ትርጓሜ ሲሆን፣ ይህም እነዚህ ማንነቶች ቋንቋዎቻቸውን፣ ባህሎቻቸውን፣ ታሪኮቻቸውና ሌሎች የማንነት መገለጫዎቻቸውን እንዲያስፋፉና እንዲያሳድጉ የሚያስችላቸው እኩል መደላድል መፍጠር ማለት ነው፡፡ ያለፉት ስርዓቶች በህዝቦች መካከል የፈጠሩትን ጥርጣሬና መራራቅ በማስወገድ ኢትዮጵያ ሁሉም ማንነቶች እኩል የሚስተናገዱባት የብሄሮች፣ ብረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ቤት እንድትሆን በማድረግ በአይነቱ የተለየ እና አስፈላጊነቱ ጥርጣሬ ላይ የማይወድቅ ግንኙነት እንዲፈጠር ማድረግ ማለት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከታሪካቸው የወረሱትን በጎ ትስስር በማጎልበት

በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አዲስ የርስ በርስ ግንኙነት መፍጠር ከፌደራላዊ ስርዓቱ መሰረታዊ አስተሳሰቦች ዋናው በመሆኑም ይህ አስተሳሰብ ከገዢ ስርዓቱ ግንዛቤን የማስጨበጥ እጥረትና ያለፉት ስርዓት ናፋቂዎች የእሩምታ ተኩሶች ተፅእኖ አንፃር የተፈለገውን ያህል ባይሆንም እስከነእጥረቱ የማይቀለበስበት ደረጃ ላይ መድረሱንና በፅኑ መሰረት ላይ መገንባቱን መካድ የማይችልና በውህደትና በመሬት ይሸጥ ይለወጥ እንዲሁም በኢትዮጵያዊነት ማስመሰያ ፕሮፖጋንዳዎች እንኳንስ ማስወገድ፤ ማነቃነቅ የማይቻልበት ደረጃ ላይ መድረሱንም ከአዲስ አበባ ወጣ ብለው ይህንኑ በፅኑ መሰረት ላይ ገንብተው ተጠቃሚ የሆኑትን የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብረሰቦችና ህዝቦች በመጠየቅና አኗኗራቸውን በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

*ይህ ማለት ግን በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ ያለፌደራላዊ ስርዓት ሃገር ማስተዳደርና መምራት እንዲሁም ህዝብን ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል መዋቅር መዘርጋት አይቻልም ማለት* አይደለም፡፡ አለመሆኑንም የአለማችንን ታሪክ ዞር ብሎ ማየትና ጥናታዊ የፖለቲካ ድርሳናትን መመልከት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያን በተመለከተ ግን ያለፌደራላዊ ስርዓት ማሰብና ማለም ከቶም አይቻልም፡፡ ያለሙትና ያሰቡትም ውድቀታቸው ጊዜ ያልወሰደበት ምክንያት ብዝሃነታችን የወለደው ግዴታና እውነታ ነው፡፡ *ይህን ብዝሃነት ያለፌደራላዊ ስርዓት መያዝና ማስተናገድ የሚቻለው ደግሞ በፌደራላዊ አስተዳደር ስርአት ብቻ ነው፤ ይህ ካልሆነ በማናቸውም አይነት ዴሞክራሲያዊ የአገዛዝ መንገድ ማስተናገድ አይቻልም።* የሚለው ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ አስተሳሰብና ላለፉት 23 ዓመታት የቆየባቸውን ከብዝሃነት ጋር የተያያዙ ሚስጥሮች እያጣቀሱ ሲያጠይቁ ለሰለምን ጥያቄዎች ምላሽ ያገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያ ህብረ ብሄራዊ የፌደራል ስርዓት ልዩ ባህሪያት ከሚባሉትና በዋናነትም ከላይ እንደተገለፀው ያለፉና የተዛቡ ግንኙነቶችን ለማስተካከል የተደነገጉና የሃገሪቱን ተጨባጭ ህብረተሰባዊ መዋቅሮች የሚያንፀባርቁ ወይም የህብረ ብሄራዊ የፌደራል ሥርዓቱን አወቃቀር የሚወስኑ ጉዳዮች ማለት እንጂ የኛዎቹ ተቃዋሚዎች እንደሚሉት ኢትዮጵያን የመገነጣጠልና የመበተን ስራ አይደለም፡፡ ይልቁንም ኢትዮጵያን ለመገነጣጠልና ለብተና የሚያበቁ ስርዓቶች ቢኖሩ ፌደራሊዝምን ባላገናዘቡ ውህደትና ፕሮፖጋንዳዎች አግባብ ለመመለስ የሚተጉ ሃይሎችን መመከትና ከማይቀለበስበት አለት ላይ መገንባት የሚያስችል አወቃቀሮችን የሚወስኑ ጉዳዮች ማለት እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

የፌደራል ስርዓቱ ልዩ ባህሪያት እንደሆኑ በህገ-መንግስታችን የተመለከቱ ነጥቦችም የመነጩበት የአስተሳሰብ ደርዝ የህዝብ ልእልናን ወይም የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችን ልዕልናን መሰረት ያደረጉ ስለመሆናቸው ህገመንግስቱን ከነባራዊው ሁኔታ ጋር አገናዝቦ በማጤን በመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከላይ እንደተገለፀውም፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች ባለፉት የዘውድና የደርጉ ስርዓቶች በሃገራቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ የተቆጠሩበት ፍፁም ፀረዴሞክራሲያዊ ስርዓቶችን ማሳለፋቸው እሙን ነው፡፡ የወቅቱ ገዢዎችና አገልጋዮቻቸው የኢትዮጵያን ህዝብ ዕድል ለመወሰን የተቀመጡ አምባገነኖች እንጂ ህዝብን ለማገልገል የተቀመጡ አልነበሩም፡፡ ስለሆነም ከአዲሲቷ ኢትዮጵያ የሚጠበቀው አንዱና መሰረታዊ ጉዳይ የጥቂቶቹን ልዕልና ያሰፈነውን ያለፈውን ስርዓትና ለውርሱ የሚተጉ ሃይሎችን በዴሞክራሲያዊ መንገድ በማስወገድ የህዝቦችን ልዕልና ማረጋገጥ እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ሃገሪቱ የምትመራባቸው መሰረታዊ መርሆዎች፣ ፖሊሲዎችና ህጎች የሚመነጩት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ፍላጎቶችን ለማሟላት ስለሆነ የመንግስት እንቅስቃሴዎችም ከዚህ አንፃር እንዲቃኙ ግድ ይላል ማለት ነው፡፡ ይህን ፈታ አድርገን ስንመለከተው የመንግስት ስልጣን፣ መንግስት የሚያራምዳቸው እምነቶች፣ የሚከተላቸው መርሆዎችና ፖሊሲዎች ምንጭ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ናቸው ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የፌደራል ስርዓቱ ልዩ ባህሪያት፣ አወቃቀር፣ የሥልጣን ክፍፍልና ትስስር መሰረታዊ መነሻ የህዝብ ልዕልና ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተቃዋሚዎቹ በፌደራላዊ ሥርዓቱ ላይ  የሚለጥፉትንና በህዝብ ስም የሚደረጉትን የምርጫ ወቅቶች ግርግሮች በሚያጋልጥ መልኩ ከወረቀት ባለፈ በተግባር በተረጋገጡ ማሳያዎች የሚገለፅ ነው፡፡ ከእነዚህም ማሳያዎች ጥቂቶቹን ከተቃዋሚዎቹ ፀረ ፌደራላዊ አስተሳሰብና ግርግር አኳያ እያንሰላሰልን መመልከት ሃቁን ለመለየት እና እውነታውን ለመገንዘብ ያስችለናል፡፡

የመጀመሪያውና የህዝብ ልዕልናን መስፈርት ላደረገው ፌደራላዊ ሥርዓቱ ሁነኛ ማሳያ የሚሆነው አሁን እያገለገለን ያለው የመንግስት መዋቅርና አወቃቀር በማንነቶች ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው፤ በማንነቶች ላይ የተመሰረተ የመንግስት አወቃቀር ሲባል ምን ማለት ነው? ተጨባጭ መገለጫውስ ምንድነው? የሚለውን ስንመለከት የምንገነዘበው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች ባለፈውና ከላይ በተመለከተው አግባብ የተነፈጉትን ማንነቶችና መብቶች፣ ታፍኖ የነበረውን ታሪካቸውና፣ ቋንቋቸውን ባህላቸውንና ሌሎች የማንነት

መገለጫዎቻቸውን በህገ-መንግስቱ ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ተፈፃሚ ማድረግ እንዲቻል የፌደራል ስርዓቱ አባል (ክልል) መንግስታት በብሄር ብሄረሰብ እንዲደራጁ ሆኖ ተዋቅሯል።

ይህ የሆነበት አቢይ ምክንያትም ለዘመናት ተዛብቶ የኖረው የርስ በርስ ግንኙነት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መወገዱን መሆኑ ስለታመነበትና በዚህ አወቃቀር አዲስ እኩልነት፣ ግንኙነትና የጋራ ህልውና እንዲመሰረት ስለወሰኑ ነው፡፡ ይህ ሃቅ በተግባር ተረጋግጦና ነባራዊው ሁኔታም የሚፈቅደው ይህንኑ ሆኖ ሳለ ይህንን አወቃቀር ለመዘርጋት የሚያስችለውን ብቸኛ የሆነ የፌደራላዊ ስርዓት አማራጭ የመበታተኛ እና የመከፋፈያ መንገድ ነው በማለትና ወደጎን በመግፋት ላሳለፍናቸው 23 አመታት ኢትዮጵያዊነትን በውዴታ ሳይሆን በግዴታ ለመጫን ከበሮ ቢደልቁምና ሙሾ ቢያወርዱም ዝቅ እንጂ ከፍ ማለት አልቻሉም፡፡ አሁን ደግሞ በውህደት ጉሮ ወሸባዬ ይህንኑ አግላይና ፀረ ዴሞክራሲያዊ የነበረውን ሥርዓት ለመመለስ አጥብቀው ቢታትሩም ዛሬም ሆነ በክፍል አንድ ፅሁፋችን ስር እንደተመለከተውና ጎምቱ የሆኑት የተቃውሞ ጎራ ፖለቲከኞቹ (ዶ/ር ነጋሶና አቶ ቡልቻ) እንዳሉት እንኳንስ የኢትዮጵያን ህዝብ ለማማለል ቀርቶ የእራሳቸውንም ዕድሜ ለወራት ማራዘም እንደማያስችላቸው ሊታወቅ ይገባል፡፡ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ‹‹ያለፌደራሊዝም ኢትዮጵያን ማሰብ አይቻልም 10 ጊዜም ቢጮህ፣ መንገዱ ጨለማ ነው›› እንዳሉ ፡፡

ሌላውና ከላይኛው ጋር የአንድ ሳንቲም ግልባጭ የሆነው የፌደራል ስርዓቱ ምንጭ የህዝብ ልዕልና ስለመሆኑ ማሳያ የሚሆነን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤት መሆናቸው ነው፡፡ በእርግጥ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ያለፌደራላዊ ሥርዓት አማራጭ መንግስታዊ ስርዓት የለም ማለት እንዳልሆነ በተመለከተው አግባብ በተለይም ባደጉት ሃገራት በተለምዶ የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት ተደርገው የሚወሰዱት ህዝቦች ናቸው፡፡ ይህ አስተሳሰብ የቡድን መብቶችን ወደጎን የተወ መሆኑን ይህንኑ አስተሳሰብ የሚያራምዱ ሃገራትን ጨምሮ በርካታ ምሁራን ይመሰክራሉ፡፡ ስለሆነም እነዚህ ሃገራት ስላደጉ ብቻ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ከእነርሱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ባላገናዘበ መልኩ የእነርሱን መንገድ መከተል እንደሚገባና የስልጣን ባለቤት ህዝቦች እንዲሆኑ በመሻት ተዋሃድን የሚሉቱ ከላይ በተመለከተው የምሁራኑ የምስክርነት አግባብ የቡድን መብቶችን ወደጎን ለመግፋት ያለሙ ስለመሆናቸው ያመላክተናል፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የሉዓላዊ

ሥልጣን ባለቤት ዜጎች ናቸው ብሎ ማለፍ በቡድን ማንነቶች ላይ ሲነሱ የነበሩ እና መስዋእትነት የተከፈለባቸውን የዴሞክራሲ ጥያቄዎች መዘንጋት ማለት እንደሆነ እሙን ነው፡፡ በአፋኝ ስርአቶች ስር ሆነው ማንነታቸውን ስለማጣት በተለያዩ ወቅቶችና ደረጃ እየተጋሉ ከመቶ ዓመታት በላይ ያሳለፉ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት ዜጎች ናቸው የሚል ድንጋጌ መቼም ቢሆን ሊቀበሉ እንደማይችሉ ግልጽ ነው፡፡

ይህን ጥያቄ ወደ ጎን የገፋውን ውህደትም፣ አቶ ሃይሉ አርአያ እንዳሉት ‹‹የተዝረከረከ›› መሆኑ ደግሞ አያጠያይቅም፡፡ ስለሆነም የአዲሲቷን ኢትዮጵያ የወደፊት እድል የመወሰን ስልጣን ባለቤት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መሆናቸውን እራሳቸው ማረጋገጣቸው ተገቢና ትክክል መሆኑ የሚያወላዳ አይደለም፡፡ ይህንን በወሰኑ ሰዓትና በምስረታው ወቅትም የገቡትን ቃል በአፈጻጸም ሂደት እንዳይዛነፍ የመጠበቅ ሃላፊነት የሚሰጣቸውን ህገመንግስት የመተርጎም ስልጣን መውሰዳቸውም የህዝብ ልዕልና ስለመሆኑ ሁነኛ ማረጋገጫ ነው፡፡ የዚህን የህዝብ ልዕልና መሰረት ያደረገው ድንጋጌ ግልጽ ትርጉምም በመከባበር፤ በመተማመንና በመተባበር በእኩልነት አብሮ የመኖር ስምምነት እንጂ በዚህና በዚያ ቢሉ ያልሰመረላቸው የግዴታ ኢትዮጵያዊነት አቀንቃኞች እንደሚሉት የመገንጣጠል ስምምነት አይደለም፡፡

*የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት* የግል መብቶችን ለማረጋገጥ ወሳኝ እንደሆነ UN Human rights Committee ይገልፃል፡፡ በርካታ ፀሃፍትም የቡድን መብቶች ከግል መብቶች ተለይተው መገደብ የሌለባቸው መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ የግል መብትን በማረጋገጥ ብቻ የቡድን መብቶችን ማረጋገጥ እንደማይችል፣ የቡድን መብቶችን የሚከለክል ስርዓት ሊሆን እንደማይችል ይጠቅሳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ያደጉ የዴሞክራሲ ሀገሮች የቡድን መብቶችን በተሟላ መልኩ ባለማረጋገጣቸው ምክንያት የቡድን መብት ጥያቄዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከሩ የሃገራቱን ውስጣዊ ሰላም በማናጋት ላይ ይገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያን ሁኔታ ስንመለከት የብሄር ብሄረሰቦች እስር ቤት ልትሆን የቻለችው የቡድን ማንነቶች መታፈን ዋነኛ የጭቆና መገለጫ ስለነበር ነው፡፡ ይህን ጭቆና በትግል በማስወገድ የራስ አስተዳደር መብትን በማረጋገጥ ብቻ የሚመለስ አልነበረም፡፡ ህገ መንግስቱን በማፅደቅ ሂደት ሲነሱ የነበሩ ጥያቄዎችና ክርክሮችን መለስ ብሎ ማሰብ ይህንን ጥያቄ ግልፅ ያደርጉታል፡፡ የአንዳንድ ብሄሮች የፖለቲካ ድርጅቶች ከጅምሩ

የመገንጠል ጥያቄ አንስተዋል፣ አንዳንዶች ደግሞ ነባሩ የተዛባ ግንኙነት በፈጠረባቸው ስነ ልቦናዊ ጫና ምክንያት በሰንደቅ ዓላማ ቀለማት አመራረጥ ሳይቀር በስፋት መከራከራቸው ይታወሳል፡፡ ይህ የሚያመለክተው ከመገንጠል በመለስ ያለውን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ማረጋገጥ ለብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በእርግጥ የሚያረካ እንዳልነበረ ነው፡፡ ካለፉት 23 ዓመታት ተጨባጭ ተሞክሮ የምንረዳው ጉዳይ የመገንጠል መብት የብሄርና ተጓዳኝ ጭቆናዎች ለማስወገድ ዋስትና ተደርጎ እንደታየ፣ እንዲሁም ይህ መብት በህገ መንግስት ከተደነገገ በኋላ ጥያቄውን ሲያነሱ የነበሩ ሃይሎች በህብረቱ መቀጠል መቻላቸውን ነው፡፡ ይህ ደግሞ የኢትዮጵያ ፌደራል ስርዓት አንዱና ልዩ ባህሪው *የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብትን* በማረጋገጥ ህብረትን ማስቀጠል መቻሉን የሚያመላክት እንጂ ለብተና የሚያበቃ አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራል ስርዓት የአመሰራረት ሂደት ሁለት ባህሪያትን ያካተተ ነው፡፡ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የደርግ ስርዓት እንደተወገደ የነበሩና ቀጥሎ የተፈጠሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በመሰረቱ በብሄራዊ ማንነት የተደራጁ ሆነው የነበሩዋቸው ዓላማዎችና ፍላጎቶች የተራራቁ ነበሩ፡፡ የአመሰራረቱ ሂደት፣ አንደኛ እነዚህን የተራራቁ ፍላጎቶች የነበሯቸው (በተናጠልም ሆነ ግንባር ፈጥረው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ) የፖለቲካ ሃይሎች ተቀራርበውና ተሰባስበው በህብረቱ እንዲቀጥሉ የተስማሙበት፣ እንዲሁም የስርዓቱ ባለቤትነት፣ ቅርፁና መሰረታዊ መርሆዎቹ በድርድርና በስምምነት ሲወሰን ማእከላዊ መንግስት እንዲኖርና ስልጣኑም በህገ መንግስቱ የተዘረዘረውን እንዲሆን የወሰኑት የብሄሮችና ብሄረሰቦች ተወካይ የፖለቲካ ሃይሎች ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ የሥልጣን ክፍፍሉን የወሰኑ ሃይሎች ነፃ መንግስታት የነበሩ ባይሆኑም ቀሪ ስልጣኖች የክልሎች እንዲሆኑ አድርገዋል፡፡ እነዚህ ምክንያቶች የሚያሳዩት አዲሱን ህብረት የመሰረቱ መሆናቸውን ነው፤ በአጭሩ እነዚህ የስርዓቱ ባህሪያት በምስረታው ወቅት ከነበሩ የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታዎች የመነጩና ሀገሪቱን ከማፈራረስ ያዳነ ስርዓት እንጂ ተዋሃድን የሚሉት እንደሚሉት አይደለም፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ ሃይማኖቶች በተለያዩ ወቅቶች ከውጭ የገቡ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ እነዚህ ሃይማኖቶች ተቻችለውና ተከባብረው ለመኖር የነበራቸውን ፍላጎት ብዙ ፈተና እየገጠማቸው ቆይተዋል፡፡ በተለያዩ ወቅቶች የነበሩ ነገስታትና ሱልጣኖች አንዱ በሌላው የበላይነት ለመቀዳጀት በእምነቶች መካከል ግጭቶችና ጦርነቶችን ይቀሰቅሱ እንደነበርም

የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ፡፡ በዚህ ምክንያት በርካታ አብያተ ክርስቲያናትና መስጂዶች ወድመዋል፤ ብዙ አማኞች ህይወታቸውን አጥተዋል፤ ይህ ብቻ አይደለም፣ በዘውድ አገዛዙ ዘመን አንድ ሃይማኖት ብቻ በሕገ መንግስት የተደገፈ የበላይነት እንዲኖረው ሁሉ ተደርጓል፤ ሌሎች አማኞች ተገድደው እምነታቸውን እንዲለውጡ ተሞክሯል፡፡ በደርግ ጊዜም ሁሉም ሃይማኖቶች እምነታቸውን በነፃነት እንዳያራምዱ ታፍነዋል፡፡

ሆኖም እኒህ እምነቶች ዘመን ተሻጋሪ የመቻቻል፣ የመከባበርና የመደጋገፍ ታሪክ አሳልፈዋል፡፡ የገዥዎችን የተሳሳተ የሃይማኖት ፖሊሲና ቅስቀሳ ወደ ጎን በመተው አንድ ሃይማኖት ከውጭ ሲመጣ በሰላም ተቀብለውና አስተናግደው እንዲኖሩ አድርገዋል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች ሃይማኖቶችን ተገን ያደረጉና ከእምነቶቹ መርህ ውጭ የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች በቀሰቀሱዋቸው ግጭቶች ምክንያት የወደሙ የሃይማኖት ተቋማትን በጋራ እየገነቡ መጥተዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያ የሃይማኖቶች የመቻቻል፣ የመከባበርና የመደጋገፍ ተምሳሌት ተደርጋ የምትወሰድ ሃገር ሆናለች፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ከተደነገጉ የህዝቦች መብቶች አንዱ የሃይማኖት እኩልነት ነው፡፡ የሚከተሉት የህገ መንግስቱ ሶስት አንቀፆች ከሃይማኖትና እምት ጋር የተያያዙ መርሆዎችና መብች አስቀምጧል፡፡ አንቀፅ 11 መንግስትና ሃይማት የተለያዩ መሆናቸውን፣ አንቀፅ 25 ሁሉም ሰዎች በመካከላቸው የዘር፣ የብሄር፣ የብሄረሰብ፣ የፆታ፣ የሃይማት ወዘተ ልዩነት ሳይደረግ እኩል የህግ ጥበቃ እንደሚደረግላቸው፣ እንዲሁም አንቀፅ 27 ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የህሊናና የሃይማኖት ነፃነት እንዳለው፣ የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት ለብቻው ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን የማምለክ፣ የማስተማርና የመግለፅ መብት እንዳለው ደንግገዋል፡፡

በእርግጥ እነዚህ መብቶች በሌሎች የዴሞክራሲ ሃገሮችም ይደነገጋሉ፤ ነገር ግን ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ድንጋጌዎች ልዩ ትርጉም የሚሰጣቸው በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛ የሃይማኖቶች እኩልነትና የእምነት ነፃነት ሳይረጋገጥ ያለፈውን የተዛባ ግንኙነት ማስተካከል አይቻልም የሚል መሰረታዊ አስተሳሰብ ስላለ፤ እንዲሁም አዲስ ኢትዮጵያዊ ማንነትን የመገንባት ጉዳይ አስፈላጊ በመሆኑ ነው። ይህ መብት መኖር የለበትም የሚል መሰረታዊ አቋም ያላቸው ወገኖች ያሉ ሲሆን ጥረታቸውም በውህደት ስምና በሰላማዊ ሰልፎ ግርግር ያለፈውን ስርአት መመለስ መሆኑም ሊሰመርበት ይገባል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች በግልም ይሁን በቡድን የመረጡትን እምነት የመከተል መብቶቻቸውን ማረጋገጥ

የህዝብ ልእልና አንድ አካል ስለሆነ  ይህም የዚሁ አካል ነው፡፡ “ኢትዮጵያን ያለፌደራሊዝም ማሰብ አይቻልም!!” ያልነውምና ወደፊትም የምንለው ከላይ በዘረዘርናቸውና ሌሎቸ ባልዘረዘርናቸው በርካታ ምክንያቶች መሆኑን እያስታወስን የዛሬውን በዚሁ አበቃን ፡ ፡